አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA


ቀን ታኅሣሥ14/2006 ዓ/ም

ቁጥር ·በ/ወቅ/12/23/2013

# ወቅታዊ መልክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

«ፈኑ እዴከ እምአርያም፣አድኅነኒ ወባልሐኒ እማይ ·ብዙኅ ፣ወእም እዴሆሙ ለደቂቀ ነኪር» /መዝ 143፥7/

በመላው ዓለም በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስር ለምትገኙ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣አበው ካህናትና ፣ ሕዝበ ክርስቲያን ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ሁላችንን በጤንነትና በሰላም ጠብቆን ለዚህች ሰዓት ስላደረሰን የአባቶቻችንን አምላክ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ይህ ወቅት በነቢያት የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባዔ መቼ እንደሚፈጸም በተስፋ ይጠባበቁበት የነበረውን ፥«ፈኑ እዴከ እምአርያም፣ አንሥእ ኃይለከ ወነዓ አድኅነነ፤ ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ» እያሉ የጸለዩበትን ያን ዘመን በማሰብ በጥልቅ መንፈሳዊ ዝግጅት ብርሃነ ልደቱን ለመቀበል የምንዘጋጅበት የጾም ወቅት ነው። በዚህ በጾማችን ወቅት የዕለት ጉርስ ፈልገው ከአገራቸው ተሰድደው ለከባድ መከራ የተጋለጡትንና በአሁኑ ወቅት ወደ ቅድስት አገር ወደ ኢትዮጵያ እየተመለሱ ያሉትን ወገኖቻችንን በጸሎታችን እና አቅማችን በፈቀደው በማናቸውም ነገር ልናስባቸው ይገባል። በብዙ መከራ ውስጥ አልፈው ለአገራቸው መሬት የበቁትንም እግዚአብሔር አምላክ በምሕረቱና በጸጋው እንዲያበረታልን ጸሎታችን ነው።

**የተወደዳችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ**

ባለፉት ወራት አጋጥሞኝ በነበረ የጤና ሁኔታ ከሩቅም ከቅርብም በጸሎትም በአሳብም በማናቸውም ነገር ከእኔ አልተለያችሁም ነበር። ከመላው ዓለም የሚመጣልኝ መልእክትም ያሳየኝ የነበረውም ይህን ነው። አሁንም ለእኔ ስላሳያችሁት መልካምነት ልዑል እግዚአብሔር በበጎነቱና በቸርነቱ እንዲያስባችሁ ጸጋውንና በረከቱን እንዲያድላችሁ ጸሎቴ ነው።

በተለይም የአትላንታ ሰዓሊተ ምሕረት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንና የአትላንታ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አበው ካህናት የቦርድ አባላትና ሕዝበ ክርስቲያን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ የሚያስፈልገውን ማናቸውንም ወጪ በመሸፈን ጊዜያችሁን ጉልበታችሁን ሳትቆጥቡ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ስትሉ የደከማችሁት ድካም ሁል ጊዜ በልቦናዬ ተጽፎ ይኖራል። ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ እና ብፁዕ አቡነ ሰላማ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን ይዘው ያሳዩኝ ፍቅር ስደቴን በረከት አድርጌ እንድቀበል፥ አምላኬ በመከራዬ ጊዜ እንዳልረሳኝም እንዳስታውስ አድርጎኛል። እንዲሁም የጤና ችግር ባጋጠመኝ ወቅት ከጎኔ ሳይለዩ ይረዱኝ የነበሩት ታላቁ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሳኤ ናቸው። እኚህ አባት ለቤተ ክርስቲያን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የደከሙትን ድካም ተናግረን አንጨርሰውም። ዛሬ ግን የምመሰክርላቸው ሰው የማያውቀውን እኔና እግዚአብሔር የምናውቀውን ነው። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እኔን እየረዱኝ ይገኛሉ፤ ዛሬም ከእኔ ጋር ናቸው።


1152 S Stone Mountain Lithonia, GA 30058 Phone: (770) 469-5462 P.O. Box 711 Stone Mountain, GA 30086

እዚህ ላይ አብሮ የሚታወስ ነገር ቢኖር ይህን ታላቅ የፍቅርና የመንፈሳዊ ተግባር እንዲያከናውኑ ከጎናቸው የቆሙት የሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ካህናት የቦርድ አባላት እና ሕዝበ ክርስቲያን ናቸው። አባ ወልደ ትንሣኤ በእነርሱ መካከል ሆነው አባታዊ ተግባራቸውን መወጣት ሲገባቸው፥ እኔን እንዲረዱኝ በመፍቀዳቸው የሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም ሕዝበ ክርስቲያንን እግዚአብሔር በእሱ በረከት እንዲባርካቸው እጸልያለሁ።

ሕመምና ስደት የተባበሩበት ሰው በመጠኑም ቢሆን ማሰቡ አይቀርም፤ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ሰው ሲሰጥ ደግሞ ኀዘንም መከራም ይረሳል። በመሆኑም በዚህ ወቅት በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስር ያሉ በመላው ዓለም ያሉ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አበው ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያን ክብር እንዲሁም ለእኔም ለጤናዬ ምቾት የሚስማማ ማረፊያና የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ገዝተዋል። በዚህ የተባበሩትን አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው እንጸልያለን።

ይህን የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት እንዲገዛ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተባበሩትን በሕጋዊ ቅ/ሲኖዶስ ስር ለዚሁ ተግባር በጠቅላይ ቤ/ክ የተቋቋመው ኮሚቴ አባላት የሆኑ ሊቃነ ጳጳሳት አበው ካህናትና ምዕመናንም ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሥራ ስለሠሩ ቤተ ክርስቲያን ታመሰግናቸዋለች። በአሁኑ ወቅት የእግዚአብሔር አጋዥነት የወላዲተ አምላክ ምልጃ ረድቶኝ እኔም በተሻለ የጤና ደረጃ ላይ እገኛለሁ። የአዲሱ የመንበረ ፓትርያርክ ሕንጻ ግዢውና እድሳት እንደተጠናቀቀ ለብፁዕ አቡነ ያዕቆብ እና ለአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህን በሰጠናቸው ትዕዛዝ መሠረት ሁሉን ነገር አዘጋጅተው እነሆ አሁን ወደ አዲሱ መንበረ ፓትርያርክ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። መንበረ ፓትርያርኩን በጥንቃቄ እድሳት እንዲደረግለትና የሚያስፈልገውም ነገር እንዲሟላለት በማድረግ የደከሙትን ብፁዕ አቡነ ሳሙኤልንና በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኙትን የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን እግዚአብሔር አምላክ ጸጋውን በረከቱን ያሳድርባችሁ እላለሁ።

በመጨረሻም ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የምናስተላልፈው መልዕክት፣ ሁላችሁ በእያላችሁበት አንድነታችሁን ጠብቃችሁ፣ በፍቅር ጸንታችሁ፣ ቤተ ክርስቲያናችሁን እየጠበቃችሁ፣ ከእለት ወደ እለት በሃይማኖት እንድትጎለምሱ አሳስባችሁአለሁ። ጥንታዊት ሐዋርያዊት የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት ጠብቀን ለማስጠበቅ የምንችለው አብረን ስንሠራ ነው። በስደትና በመጻተኛነት በምንኖርበት ምድር የእግዚአብሔርን መንግሥት እየናፈቅን፣ የወንጌልን አደራ እየጠበቅን ወደፊት ልንሄድ ይገባል። አምላከ ቅዱሳን ሁላችንም በያለንበት ይጠብቀን። ጾማችንንና ጸሎታችንን ወዶ ይቀበልልን። ለብርሃነ ልደቱም በሰላም ያድርሰን። አሜን።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ይባርክ።

አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ